Equal Rights Center

FAIRNESS & EQUALITY IN HOUSING, EMPLOYMENT, PUBLIC ACCOMMODATIONS & GOVERNMENT SERVICES

est. 1983

*Advancing Civil Rights For Over a Quarter Century*

# የመኖሪያ ቤትን ተደራሽ ማድረግ




## አሳማኝነት ያላቸው ማስተካከያዎች/ማሟያዎች እና ማሻሻያዎች መመሪያ

# ሲቪል መብቶች ምርመራ

የሰብዓዊ መብቶች ፍተሻ/ምዘና አብዛኛውን ጊዜ የሚታዩ ባህሪዎችን ከሕጋዊ መስፈርቶች ወይም ከፖሊሲ ጋር ለማነጻጸር መረጃ ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የሚውል የምርመራ መሳሪያ ነው። ይህም አንድ ወይም ሁለት ሰዎች በምስጢር የሚያደርጉትን ዝውውር ወይም መስተጋብር ያካትታል። ተመሳሳይ የሆነ ጥምረት ፍተሻ አንድ የሰብዓዊ መብቶች ፍተሻ ዓይነት ሲሆን፣ ሁለት ሰዎች ያሏቸው ሁሉም መስፈርቶች በሙሉ ተመሳሳይ ሆነው ባላቸው አንድ መስፈርት ላይ ተመስርቶ በመካከላቸው የሚደረገውን የአያያዝ/የማስተናገድ ልዩነት ያነጻጽራል፥







የሰብዓዊ መብቶች ፍተሻ ለሚከተሉት ነገሮች ጠቃሚ መሳሪያ ነው፥

www.equalrightscenter.org

- ህብረተሰቡን ለማስተማር
- የፖሊሲ አድቮኬሲን ለመደገፍ
- ድርጅቶችን ለማሰልጠን
- ህግን ለማስፈጸም

# ማውጫ


ዳራ ..... 2

ማስተካከያዎች/ማሟያዎች ..... 3

አሳማኝነት ያለው ምንድን ነው? ..... 4

የግንኙነት ሂደት ..... 5

የህግ ጥበቃዎች ..... 7

የመድልዎ ምልክቶች/ መገለጫዎች ..... 8

ምን ማድረግ ይችላሉ ..... 9

ናሙና ደብዳቤ ..... 10

እርዳታ እንዴት ማግኘት ይችላሉ ..... 13



The Equal Rights Center 2018 – መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው



ለዚህ ህትመት መሰረት የሆነው ስራ በአሜሪካ የቤቶች እና የከተማ ልማት መምሪያ በኩል የተገኘ የገንዘብ እርዳታ የተደገፈ ነው። የስራው ፍሬ ነገር እና ውጤቶች መታሰቢያነታቸው ለህዝብ ነው። በዚህ ህትመት ውስጥ ለተነገሩ መግለጫዎች እና መግለጫዎቹ የሚሰጡት ትርጓሜ ሙሉ ሃላፊነት የደራሲው እና የአሳታሚው ነው። እንደነዚህ አይነት ትርጓሜዎች የፌዴራል መንግስትን አመለካከቶች የግድ ያንፀባርቃሉ ማለት አይደለም።


በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተተው መረጃ ህጋዊ ምክር ስላልሆነ፣ በዚህ መልኩ መወሰድ የለበትም። ለህጋዊ የምክር አገልግሎት፣ እባክዎትን ጠበቃ ያነጋግሩ።

# ዳራ

አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች በመረጡት ማህበረሰብ ውስጥ የመኖር መብት አላቸው። የሲቪል መብቶች ህጎች የተዘጋጁት አካል ጉዳተኛ ሰዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ሰዎች ጋር እኩል መኖሪያ ቤት የማግኘትና የመጠቀም መብት እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነው። ከዘርፈ ብዙ አገልግሎት ሰጪ መኖሪያ ቤቶች ዲዛይን እና ግንባታ ጋር ተያያዥነት ካላቸው መስፈርቶች በተጨማሪ የፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት ህግ አካል ጉዳተኛ የሆኑ ሰዎች መኖሪያ ቤታቸውን በተሟላ ሁኔታ ለመጠቀምና ለመገልገል ይችሉ ዘንድ አሳማኝ ማስተካከያዎች/ማሟያዎች እና/ወይም ማሻሻያዎች እንዲደረግላቸው እንዲጠይቁ ይፈቅድላቸዋል። ይህ በራሪ ጽሁፍ እነዚህን መብቶች እና መብቶቹን እንዴት እንደሚጠይቁ በመግለጽ ይረዳዎታል።

አካል ጉዳተኛ ሰዎች የተለያዩ ባህሪያት ያላቸው ሲሆኑ አንዳንድ ጊዜ አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው ባህሪ የታወቀ ነው። በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ ላይታወቅ ይችላል። አካል ጉዳተኝነት ከእንቅስቃሴ፣ አቀባበልና ምክንያታዊነት፣ የስሜት ህዋስ፣ ስነ ልቡና፣ እድገት/አስተዳደግ፣ ወዘተ ጋር የተያያዘ ሊሆን ይችላል። አካል ጉዳት በተጨማሪም ጊዜያዊ፣ ዘላቂነት ያለው እና/ወይም በጊዜ ሂደት የሚቀየር ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው በተጨማሪም ከአንድ በላይ ማስተካከያ/ማሟያ ወይም ማሻሻያ የሚፈልጉ ከአንድ በላይ አካል ጉዳቶች ሊኖሩበት ይችላሉ።

አካል ጉዳት ካለብዎ ማስተካከያ/ማሟያ ወይም ማሻሻያ የመጠየቅ መብት አልዎ። ጥያቄው ወደ መኖሪያ ቤት ከመግባቱ በፊት ወይም ወደ መኖሪያ ቤቱ ከገቡ በኋላ በየትኛውም ጊዜ ሊቀርብ ይችላል። በተጨማሪም ከአንድ በላይ ጥያቄዎችን ሊያቀርቡ ወይም ጥያቄውን ያቀረቡባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚቀየሩ ከሆነ በጥያቄዎ ላይ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ። በአብዛኛው ተከራዮች ለአከራዮች ወይም የመኖሪያ ቤት ሥራ አስኪያጆች ጥያቄ የሚያቀርቡ ቢሆንም አካል ጉዳተኛ የሆኑ የቤት ባለቤቶች እንደ የመኖሪያ ቤት ማህበራት ወይም የማዘጋጃ ቤት አስተዳደሮች ላሉ ተቋማት የምክንያታዊ ማስተካከያ እና/ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ።

# ማስተካከያዎች/ማሚያዎች




## አሳማኝነት ያላቸው ማስተካከያዎች/ ማሚያዎች



ማስተካከያ ማለት አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው እኩል የመኖሪያ ቤት የመጠቀምና የመገልገል እድል እንዲያገኝ የሚያስችል የህግ፣ ፖሊሲ፣ አሰራር ወይም አገልግሎት ለውጥ ነው። የዚህ ምሳሌዎች በቂ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ማዘጋጀትን ወይም «የቤት እንስሳት ማሳደግ በማይፈቀድበት» መኖሪያ ቤት ውስጥ የእንስሳት እርዳታ መፍቀድን ያጠቃልላሉ።

## አሳማኝነት ያላቸው ማሻሻያዎች



ማሻሻያ በጠቅላላው የቤት፣ የጋራ መገልገያ ቦታ እና/ ወይም የማህበረሰብ መገልገያ ቦታ ላይ የሚደረግ መዋቅራዊ ለውጥ ነው። ማሻሻያዎች አንድን ቦታ አካል ጉዳተኛ ለሆነ ሰው ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ ያሻሽላሉ። ምሳሌዎች የእጅ መደገፊያ ብረት፣ መወጣጫ መትከልን ወይም መሰናከል የሆኑ ወይም ከልክ በላይ የተዘረጉ ነገሮችን ማንሳትን ያጠቃልላሉ። መኖሪያ ቤቱ በፌደራል ደረጃ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ወይም የምቹ ተደራሽነት ዲዛይን ደረጃዎችን የማያሟላ ካልሆነ በስተቀር አንድ ተከራይ የማሻሻያውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት ሊኖርበት እና ከቤቱ ሲወጣ ቤቱን በነበረበት ሁኔታ መልሶ ማስተካከል ሊኖርበት ይችላል።

# አሳማኝነት ያለው ምንድን ነው?



የተጠየቀው ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

1. በጥያቄውና በግለሰቡ አካል ጉዳተኝነት መካከል ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል ግንኙነት - ተያያዥነት መኖር አለበት።
2. በመኖሪያ ቤት አቅራቢው ላይ ያልተገባ የገንዘብ ወይም አስተዳደራዊ ጫና መፍጠር የለበትም፣ ወይም በአገልግሎቶቹ ላይ መሰረታዊ ልዩነትየሚያመጣ መሆን የለበትም።

አገልግሎት ወይም ማሻሻያ በሚጠይቁበት ጊዜ ምንም እንኳን ጥያቄው የሚቀርበው ለታወቀ አካል ጉዳት ከሆነ ተፈጻሚነት የሌለው ቢሆንም ጥያቄዎን የሚደግፍ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ አለብዎ። ዶክተሮችን፣ ነርሶችን፣ የጉዳይ ሰራተኞችን፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎችን እና ጠበቆችን ጨምሮ የሰነድ ማስረጃ ከተለያዩ ምንጮች ሊቀርብ ይችላል። አንድ የቤት አቅራቢ የተወሰነ አይነት የሰነድ ማስረጃ መጠየቅ የማይችል ሲሆን ዝርዝር የህክምና መረጃዎን መግለጽ አይጠበቅብዎትም።




አንዳንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢዎች አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ጥያቄ ለማቅረብ የተወሰነ ቅጽ ወይም ሂደት እንዲጠቀሙ ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ጥያቄያቸውን ለማስተናገድ ሊመርጡ የሚችሉ ቢሆንም ይህ የግድ አይደለም። ጥያቄዎችን በጽሁፍ ማቅረብ በአግባቡ የተገመገመና የተፈቀደ ጥያቄዎ ላይ ማንኛውም አይነት መሰናክሎች የሚያጋጥሙዎ ከሆነ እንደ የመዝገብ ማስረጃ ሆኖ ያገለግልዎታል።

# የግንኙነት ሂደት



አንድ ሰው አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ መጠየቁ እና የመኖሪያ ቤት አቅራቢው ለጥያቄው በሚሰጠው መልስ ላይ የግንኙነት ሂደት ማካተት አስፈላጊ ነው።

የግንኙነት ሂደት ከድርድር የተለየ ነው። አንዴ ጥያቄው ከቀረበ በኋላ የመኖሪያ ቤት አቅራቢው



የጥያቄውን አስፈላጊነት፣ እና ጥያቄው ያልተገባ የገንዘብ ወይም አስተዳደራዊ ጫና ስለመፍጠር አለመፍጠሩ ወይም በአገልግሎት ላይ መሰረታዊ ለውጥ ስለማምጣት አለማምጣቱ መገምገም አለበት። ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ወይም የመኖሪያ ቤት አቅራቢው የተወሰ ጥያቄ ላይ ችግር ካለበት አካል ጉዳተኝነት ያለበት ሰው ለመጀመሪያው አሳማኝነት ያለው የማስተካከያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄው ተጨማሪ ማስረጃ ወይም ማሻሻያ የሚያቀርብበት እድል ማግኘት አለበት።



የስኬታማ የግንኙነት ሂደት ውጤት ተከራዮች የፈለጉትን ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ በትክክል ማግኘታቸው ብቻም ሳይሆን ተነጋጋሪ ወገኖች አካል ጉዳተኝነት ላለበት ሰው በቤት አቅራቢው ላይ ያልተገባ ጉዳት ሳይደርስ መኖሪያ ቤቱን እንዲጠቀምና እንዲገለገል የሚያስችል መፍትሄ ላይ መድረሳቸውም ጭምር ነው።

# የግንኙነት ሂደት



## የአርኤ/አርኤም ጥያቄ አስፈላጊ ክፍሎች

አሳማኝነት ያለው የማስተካከያ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ወቅት ማቅረብ የሚጠበቅብዎ የሚከተሉትን የሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ ብቻ ነው፡-

- አካል ጉዳተኝነቱ የማይታወቅ ከሆነ አካል ጉዳተኝነት ያለብዎ መሆኑን፣
- የማይታወቅ ከሆነ በጥያቄዎ እና አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ/ማሻሻያ መካከል ያለውን ግንኙነት።

አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ አሳማኝነት ያለውን የማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ጥያቄ ለመቀበል የሚከተሉትን እንዲያቀርቡ ሊጠይቅዎት <u>አይችልም፡-</u>

- የህክምና ሪከርዶችዎን
- ህክምናዎን፣ የአካል ጉዳተኝነት ደረጃዎ ክብደትን እና/ወይም ዘላቂነትን የተመለከተ መረጃ
- ለመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ ዶክተርዎን ወይም የህክምና አገልግሎት አቅራቢዎን እንዲያናግር ፍቃድ እንዲሰጡ
- የቤት እንስሳዎ እገዛ የሚያደርግልዎ መሆኑን ወይም የተወሰነ ስልጠና መውሰዱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ (የቤት እንስሳ እገዛ ጥያቄ የሚያቀርቡ ከሆነ)

# የህግ ጥበቃዎች



## የፍትሀዊ የመኖሪያ ቤት ህግ

በአንድ ሰው የሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ ከመኖሪያ ቤት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ልውውጦች ላይ መድልዎ መፈጸምን ይከለክላል:

- አካል ጉዳተኝነት
- ዘር
- ቀለም
- ብሄራዊ ማንነት
- ሀይማኖት
- ጾታ
- የቤተሰብ ደረጃ (ቤተሰቡ እድሜያቸው ከ18 አመት በታች የሆኑ ልጆች ያለው መሆን አለመሆኑ)

በህጉ የተከለከለ አንዱ የአካል ጉዳተኝነት መድልዎ አይነት አገልግሎቶች አካል ጉዳተኛ የሆነ ሰው እኩል በመኖሪያ ቤት የመጠቀምና የመገልገል እድል እንዲያገኝ ለማድረግ አስፈላጊ ከሆኑ በአገልግሎት ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ አሰራሮች ወይም ማስተካከያዎች ላይ ለውጥ ለማድረግ ፍቃደኛ አለመሆን ነው።

## አካል ጉዳተኛ የሆኑ አሜሪካውያን ሕግ (ኤዲኤ)

የአሜሪካውያን አካል ጉዳተኞች ህግ ከሚደነግጋቸው ጥበቃዎች ውስጥ አንዱ የማህበረሰብ መገልገያ ቦታዎች በመዋቅርና ፕሮግራም ደረጃ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሰዎች ተደራሽ መሆን እንዳለባቸው ነው። ተደራሽ መሆን ያለባቸው ቦታዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-

- በመኖሪያ ቤት ግንባታዎች ውስጥ ያሉ እንደ የሊዝ ቢሮዎች፣ የህዝብ መገልገያ ሽንት ቤቶች እና የጋራ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ያሉ የህዝብ መገልገያ ቦታዎች፣ እና
- በግዛት ወይም የአካባቢ አስተዳደር የሚተዳደሩ የህዝብ መኖሪያ ቤቶች

## የማቋቋሚያ ህግ ክፍል 504

የትኛውም በዩ.ኤስ የመኖሪያ ቤትና ከተማ ልማት መምሪያ (ኤችዩዲ) አማካኝነት የፌደራል የገንዘብ ድጋፍ የሚያገኝ የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን አካል ጉዳተና ለሆኑ ሰዎች ተደራሽ መሆን አለበት።

- ይህ የማህበረሰብና የብዙ ቤተሰብ የመኖሪያ ቤት ፕሮጀክቶችን ያጠቃልላል።

# የመድልዎ ምልክቶች/ መገለጫዎች

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ እገዛ ለሚያደርግልዎ እንስሳ ክፍያ ሊያስከፍልዎ ይችላል ወይም እንስሳው ልዩ ስልጠና ስለመውሰዱ የሚያረጋግጥ የተወሰነ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ሊጠይቅዎ ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ለድጋፍ ሰጪ እንስሳዎ ፍቃድ ሊሰጥዎ የሚችለው የህንጻው የቤት እንስሳት ማርባት፣ ክብደት ወይም መጠን ገደቦች ከተሟሉ ብቻ ነው።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ሌላ ቦታ ቢኖሩ የተሻለ ነው ብሎ እንደሚያስብ ሊነግርዎ ወይም የገለጹለትን ሌሎች አሳማኝ ምርጫዎችዎን በቸልተኝነት ሊያልፋቸው ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ለጥያቄዎ ምንም መልስ ላይሰጥዎ ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ አሳማኝነት ያለው የማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ጥያቄዎን ለመቀበል የመረጣቸውን ቅጾች እንዲያቀርቡ ሊጠይቅዎ ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ጥያቄዎን ካቀረቡ በኋላ ሊተነኩስዎ ወይም በአካል ጉዳተኝነትዎ ሊያሾፍ ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ ስለ አካል ጉዳተኝነትዎ ህጋዊነት ሊጠይቅዎ ይችላል።

- አንድ የመኖሪያ ቤት አቅራቢ አሳማኝነት ያለው ማሻሻያዎን በሚያሰሩበት ወቅት የመረጠውን ተቋራጭ ወይም እቃዎች እንዲጠቀሙ ሊጠይቅዎት ይችላል።

# ምን ማድረግ ይችላሉ



እርስዎ ወይም የእርስዎ የቤተሰብ አባል አካል ጉዳተኝነት ካለባችሁ ፍላጎትዎን የሚያሟላ መኖሪያ ቤት ማግኘት ፈታኝ ሊሆን ይችላል። ይህን የማግኘት መብቶች እንዳሉዎና በዚህ ላይ እገዛ የሚያደርጉልዎ ድርጅቶች እንዳሉ ያስታውሱ!

የሚከተሉት አሳማኝነት ያለው ማሻሻያ ወይም ማስተካከያ ሲፈልጉ መከተል የሚችሏቸው ጥቂት ደረጃዎች ናቸው፡-

- ችግርዎን ለይተው ይወቁ – ከመኖሪያ ቤት አቅራቢዎ የትኛውም ፖሊሲዎች ላይ እንዲቀየር የሚፈልጉትን ነገር ምስል ያንሱ፣ የጽሁፍ ማብራሪያ ያዘጋጁ፣ ወይም ማስታወሻ ይያዙ።
- አከራይዎን ወይም የንብረቱን ስራ አስኪያጅ ያናግሩ – የሚጠይቁትን ማስተካከያ ወይም ማሻሻያ ያብራሩ። ስለሚናገሩት ነገር ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በቀጣዩ ክፍል ላይ ያሉትን ምሳሌዎች ይመልከቱ።
- ዝርዝር ማስታወሻዎች ይያዙ – ጥያቄዎን በተመለከተ ያደረጓቸውን እንደ ኢሜይል እና/ወይም የውይይት ማስታወሻ ያሉ ግንኙነቶች ኮፒዎችን ያስቀምጡ።
- ሎጥያቄዎ ምላሽ ወይም ተቀባይነት ካላገኙ እገዛ ለማግኘት ERCን ያነጋግሩ።

# አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ ደብዳቤ

ጃኑዋሪ 1፣ 2018

ውድ የንብረት አስተዳዳሪ፣

ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ውስጥ ባለው የኤቢሲ አፓርትመንትስ 3ኛ ፎቅ ላይ ባለው በዩኒት 300 ውስጥ ነዋሪ ነኝ። ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው አሳማኝነት ስላለው ማስተካከያ ጥያቄ ለማቅረብ ነው። በደረጃዎች ላይ መውጣት እና መውረድን አስቸጋሪ የሚያደርግብኝ የአካል ጉዳት ሁኔታ አለብኝ። የማቀርበው ጥያቄም አንደኛ ፎቅ ላይ የሚገኝ ቀጥሎ ወደሚለቀቅ ባለአንድ መኝታ ቤት ውስጥ ለመግባት ሲሆን፣ ይህም ወደክፍሌ በየጊዜው ሁለት ፎቆ መውጣት እና መውረድን ያስቀርልኛል። እባክዎትን ቤት ለመቀየር ያቀረብኩት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ እንደሆነ ወይም አላገኘ እንደሆነ እስከ ጃኑዋሪ 30፣ 2018 ድረስ ያሳውቁኝ።

ከሰላምታ ጋር፣

Jane Doe

Jane Doe

# አሳማኝነት ያለው ማሻሻያ ደብዳቤ

ጃኑዋሪ 1፣ 2018

ውድ የንብረት አስተዳዳሪ፣

ዋሽንግተን ዲ.ሲ. ውስጥ ባለው የኤክስዋይዜድ አፓርትመንትስ ወደሚገኘው ዩኒት 100 በፌብሩዋሪ 15፣ 2018 ላይ ገብቼ መኖር እጀምራለሁ። ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው አሳማኝነት ስላለው ማሻሻያ ጥያቄ ለማቅረብ ነው። የአካል ጉዳተኛ ስሆን ተሽከርካሪ ወንበር/ዊልቼር ተጠቃሚ ነኝ። በመሆኑም፣ መኖሪያ ቤቴን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም እደሰትበት ዘንድ ለመቻል እንዲረዳኝ ከካውንተሮቹ ስር ያሉትን ካቢኔቶች ለማፍረስ እና ቁመታቸውን ለማሳጠር እፈልጋለሁ። ይህንን አሳማኝነት ያለው ማሻሻያ ለማድረግ እና፣ ቤቱን ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት የቤቱን ካቢኔቶች መጀመሪያ ወደነበሩበት ይዞታ ለመመለስ የሚያስፈልጉትን ወጭዎች ለመሸፈን ዝግጁ ነኝ። እባክዎትን አሳማኝነት ላለው ማሻሻያ ያቀረብኩት ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ እንደሆነ ወይም አላገኘ እንደሆነ እስከ ጃኑዋሪ 30፣ 2018 ድረስ ያሳውቁኝ።

ከሰላምታ ጋር፣

Jane Doe

Jane Doe

# የደብዳቤ አብነት/ቴምፕሌት

ቀን

ውድ የንብረት አስተዳዳሪ፣

በአሁኑ ሰዓት በ (አድራሻ) ውስጥ ነዋሪ ነኝ። ይህንን ደብዳቤ የምጽፈው አሳማኝነት ስላለው ማስተካከያ ጥያቄ ለማቅረብ ነው። የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያስከትል (አሳማኝነት ስላለው ማስተካከያ እንዲጠይቁ የሚያደርጉዎት ምክንያቶች) የአካል ጉዳት ሁኔታ አለብኝ። ለአካል ጉዳት ሁኔታዬ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ከ (ሃኪም/ቴራፒስት/የማህበራዊ ሰራተኛ ስም) ሰነድ አያይዣለሁ።* (ችግሮቹ) በ (የተጠየቀው አሳማኝነት ስላለው ማስተካከያ) አማካይነት ሊቃለሉ ይችላሉ። (የተጠየቀው አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ) እንደሚያስፈልገኝ ማስረጃ ይሆን ዘንድ ከ (ሃኪም/ቴራፒስት/የማህበራዊ ሰራተኛ ስም) ሰነድ አያይዣለሁ።** እባክዎትን ለ (የተጠየቀው አሳማኝነት ያለው ማስተካከያ) ተቀባይነት አግኝቶ እንደሆነ ወይም አላገኘ እንደሆነ እስከ (ቀን) ድረስ ያሳውቁኝ።

ከሰላምታ ጋር፣

የእርስዎ ስም

*ይህ የሚያስፈልገው የአካል ጉዳትዎ ግልጽ ካልሆነ ብቻ ነው

** ይህ የሚያስፈልገው በአካል ጉዳትዎ እና ባቀረቡት ጥያቄ መካከል ያለው ግንኙነት ግልጽ ካልሆነ ብቻ ነው

# እርዳታ እንዴት ማግኘት ይችላሉ

መድልዎ አጋጥሞኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣ ቅሬታዎን ለዩ.ኤስ የመኖሪያ ቤት እና ከተማ ልማት መምሪያ (ኤችዩዲ) ወይም በአካባቢዎ ባለው የሚመለከተው የቤት ምርመራዎች የሚያካሂድ የመንግስት ኤጀንሲ በኩል ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት።

ERC ታላቁን የዋሽንግተን ዲ.ሲ. ክልል ለማገልገል ተግቶ የሚሰራ ብቸኛው ፍትሃዊ የግል የመኖሪያ ቤት ድርጅት ሲሆን፣ በአካባቢው የቤት አድልዎ ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ግለሰቦችን የሚከተሉትን በማድረግ ሊረዳ ይችላሉ፥

- የሲቪል መብቶች ፍተሻ በማድረግ
- የቤቶች መገለል ቅሬታን ለኤችዩዲ ወይም ለግዛቱ/አከባቢያዊ ኤጄንሲዎች በማመልከት ረገድ እገዛ በማድረግ
- አሳማኝነት ያላቸውን ማስተካከያዎች እና/ወይም ማሻሻያዎች አስመልክቶ ከቀረቡ ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ እርስዎን በመወከል መነጋገር
- ሌሎች የአካባቢ አማራጮችን በተመለከተ ጥቆማ መስጠት።

## THE EQUAL RIGHTS CENTER

ስልክ ቁጥር- 202-234-3062 / የነጻ ጥሪ ቁጥር- 866-549-0009 / ሪሌይ- 711
www.equalrightscenter.org / info@equalrightscenter.org

The Equal Rights Center (ERC) በዋሽንግተን ዲ.ሲ. እና በሀገር አቀፍ ደረጃ በመኖሪያ ቤት፣ የስራ ቅጥር እና ለማህበረሰብ በሚቀርቡ የመንግስት አገልግሎቶች ላይ የሚፈጸም ህገወጥና ፍትሀዊነት የጎደለው መድልዎን ለማስቀረት የተቋቋመ የሲቪል መብቶች ድርጅት ነው።

ERCህገወጥና ኢ -ፍትሀዊ መድልዎን ለይቶ ለማወቅ የሚጠቀምበት መሰረታዊ ስትራቴጂ የሲቪል መብቶችን መመርመር ነው። ERC የተፈጸመ መድልዎ መኖሩን ለይቶ ሲያውቅ ይህን የምርመራውን ዳታ ተጠቅሞ መንግስትና የንግዱን ማህበረሰብ በማስተማር፣ ለመንግስት ግንዛቤ ማስጨበጫ ድጋፍ በማድረግ፣ የተሟላ ምርመራ በማድረግ እና አስፈላጊ ከሆነ የማስፈጸሚያ እርምጃ በመውሰድ ለማስቀረት ይሰራል።


## THE EQUAL RIGHTS CENTER

ስልክ ቁጥር- 202-234-3062

የነጻ ጥሪ ቁጥር- 866-549-0009

ሪሌይ - 711

www.equalrightscenter.org
info@equalrightscenter.org